# ልጅ ኢያሱና አጼ ኃይለሥላሴ

## ገላውዴዎስ አርኣያ

November 27, 2007

ከዚህ ቀደም በተከታታይ ስለ አጼ ቴዎድሮስ፡ አጼ ዮሃንስና አጼ ምንሊክ አጭር የሒወት ታሪካቸውና ኢትዮጵያን በመምራትና ወደፊት ለማራመድ ላደረጉት ጥረት በዚሁ በአፍሪቃ ልማትና ትምህርት ተቋም (አልትተ) አቅርብያለሁ። አሁን ደግሞ የሕብረተሰባችን አባላት፡ በተለይም መምህራንና ተማሪዎች፡ ነቀፌታ-አዘል በሆነ መልኩ እንድያጠኑትና እንዲመራመሩበት የልጅ እያሱና አጼ ኃይለሥላሴ አቀርባለሁ።

ስለ አጼ ኃይለሥላሴ አያሌ መጻሕፍት ተጽፏል፣ በርካታ ደራስያንም በተለያየ መልክ ስለ ሕይወት ታሪካቸው መዝግበውታል። ንጉሠ ነገሥቱም ሳይቀሩ ‘ሕይወቴና የኢትዮጵያ እርምጃ’ በሚል ርእስ በጻፉት መጽሓፍ ስለራሳቸውና ተሞክሯአቸው እንዲሁም ኢትዮጵያን ለማበልጸግ ያደረጉት ጥረት መዝግበውታል። ስለ ልጅ እያሱ ግን እምብዛም የሚታወቅ ነገር የለም፣ ግፋ ቢል የሕይወታቸው ታሪክ በሚመለከት አሉታዊ በሆነ መንገድ ነው የሚቀርበው። በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ አስጸያፊና ወራዳ ስም ይዘው ያለፉት ልጅ (አቤቶ) እያሱ ናቸው። ይህ ግን ትክክል እንዳልሆነ ዝቅ ብለን እንመለከተዋለን።

እኔ በበኩሌ እንደ አውሮጳ አቆጣጠር በ1995 ዓ.ም. ‘ኢትዮጵያ፣ የፖለቲካ ኢኮኖሚ ሽግግር’ በሚል ርእስ በጻፍኩት መጽሓፍ፣ በሁለተኛው ምዕራፍ፣ “አጼ ኃይለሥላሴና የኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄ” ውስጥ ስለ ንጉሠ ነገሥቱ ሰፋ ባለ መልክ አቅርቤዋለሁ፣ ስለ ልጅ እያሱ ግን አሁን ለመጀመርያ ግዜ ነው የምጽፈው ያለሁት።

ስለ ልጅ እያሱ ታሪካዊ ሰነዶች፡ መዛግብትና መጻሕፍት ሊታተሙና ሊወጡ ያልቻሉበት ምክንያት የሳቸው ባላንጣ የሆኑት አጼ ኃይለሥላሴ ለሓምሳ ዓመታት ያህል (በልዑል አልጋወራሽነትና በንጉሠ ነገሥትነት) በትረ ሥልጣኑን ስለጨበጡና፣ መደበኛ ታሪክም ብዙውን ግዜ በሥልጣን ላይ በተቀመጠውና በተከታዮቹ (ጋሻ ዣግሬዎቹ) ስለሚጻፍና ትክክለኛና ሓቀኛ ታሪክም ሊመዘገብ ስለማይቻል ነው።

በባህላችን ይሁን በትላልቅ ኃይማኖቶች ዘንድ ሓቅን መናገር በከፍተኛ ደረጃ የሚታይና የግለሰቦች ጠንካራ ጎን የሚንጸባረቅበት ነው ተብሎ በሰፊው ይነገራል። ባሁኑ ግዜ ግን የሓቅ ወዳጆች ቍጥራቸው በጣም አነስተኛ ሆኖ የእውነት ጠላቶች ግን እልፍ አእላፍ ናቸው ቢባል ማጋነን አይሆንም። ሓቅ ግን በግዝያዊ መልክ ትጠፋ እንደሆነ እንጂ አትሞትም። ስለሆነም ይኸንን እምነት በመንተራስ የልጅ እያሱና የአጼ ኃይለሥላሴ ታሪክ ፍርጥርጥ አድርጌ ለማቅረብ በዚሁ ጽሑፍ ሞክርያለሁ።

የዚህ ርእሰ-ነገር ዋና ዓላማ ግን ‘ያበጠውን ይፈንዳ’ ሳይሆን፡ ከፍ ብሎ እንደተጠቀሰው የኢትዮጵያ ተማሪዎች፡ ምሁራንና ተማራማሪዎች እንደ ገበታና መድረክ እንዲገለገሉበት ነው። በዚህ ጽሑፍ ውስጥ፡ የሁለቱ የኢትዮጵያ መሪዎች አንጻራዊ፡ ሚዛናዊና ሂሳዊ በሆነ መንገድ ለማቅረብ ይመች ዘንድ ሁለት ኢትዮጵያውያን ደራስያን፡ ማለትም አቶ ዘውዴ ረታና አቶ ጕበዜ ጣፈጠ በጻፏቸው መጻሕፍት ላይ በመንተራስ ለአንባቢ አቀርባለሁ። የአቶ ዘውዴ መጽሓፍ ‘ተፈሪ መኰንን፡ ረዥሙ የሥልጣን ጉዞ’ በሚል ርእስ የወጣ ሲሆን፣ የአቶ ጕበዜ ጣፈጠ ደግሞ ‘አባ ጤና ኢያሱ’ በሚል ርእስ የቀረበ ነው።

መጀመርያ አቶ ዘውዴ ረታ ስለ ልጅ ኢያሱ ያቀረቧቸውን ሐተታዎች ወይም ሌሎች ሰዎች ስለ አቤቶ ኢያሱ ያሉትንና ደራሲው የመዘገቡትን ላቅርብና ቀጥየ ከአቶ ጕበዜ ከተቹትና ካጠናከሩት ትዝብቶች ጋር አወዳድራቸዋለሁ። አንባቢም የራሱን አስተያየት፡ ትዝብትና ፍርድ ይሰጥ ዘንድ ሆን ብየ ክፍት መድረክ ለማቅረብ እሞክራለሁኝ።

በገጽ 88 አቶ ዘውዴ ስለ ኢትዮጵያ አንድነት በሚመለከት፣ እኔም ብዙ ግዜ በመደጋገም የጻፍኩበት፣ አጼ ምንሊክ ለኢትዮጵያ ሕዝብ አደራ ያሉትን በእንዲህ መልክ አስፈረውታል፦

“ከዚህ ቀደም በገገርዎች አለማወቅ በሕዝቡ አለመስማማት፣ ለብዙ ዘመናት ተከፋፍላ የነበረችውን አገራችን ኢትዮጵያን፣ ተጣጥሬ አንድ አድርጌ አስፍቻታለሁ። እናንተም ከልጄ ጋር ሆናችሁ፡ ተስማምታችሁና ተሳስባችሁ፡ የኢትዮያን ድንበር እንዲሰፋ እንጂ እንዳይጠብ፡ አንዲትም ቅንጣት መሬት በውጭ ጠላት እንዳይወሰድ አድርጉ።...እናንተ አንድ ልብ ባለመሆን በምቀኝነት እርስ በርሳችሁ ካልተላለቃችሁ በስተቀር፡ ኢትዮጵያን የውጭ ባዕድ አይደፍራትም። ክፉም አያገኛትም።” አጼ ምንሊክ።

አጼ ምንሊክ ብልህና አስተዋይ ስለነበሩ የዛሬ መቶ ዓመት የተናገሩትን ላሁኑ ትውልድ የቀረበ ምክር ነው የሚመስለው። ምክራቸውን ልጠቅሰው የፈለግኩትን ዋና ምክንያት ግን ‘ከልጄ ጋር ሆናችሁ’ የሚለውን ‘ልጅ ኢያሱን’ ማለታቸው ለመሆኑ ለማስታወስ ነው። ምክንያቱም አጼ ምንሊክ በአዋጅ በነጋሪት ጃን ሜዳ ለተሰበሰበው ሕዝብ በግንቦት 10 1901 ዓ.ም. አቤቶ ልጅ ኢያሱ የአልጋ ወራሻቸው መሆናቸውን አስታወቁ። አቶ ጕበዜም በገጽ 50 እንዳመለከቱት አጼ ምንሊክ እንዲህ ይላሉ፦

“አሁንም እኔ እንደተመኘሁት እግዚአብሔር የተጨመረበትና ፈቃዱ ሆኖ ልጄን ኢያሱን ቢያቆይላችሁ ከልጄ ጋር ሆናችሁ አገራችሁን ጠብቁ፣ አደራ ብያችኋለሁ። አደራ የሚያኖሩበት ሰው የታመነ ስለሆነ ነው። አሁንም እኔ እናንተን አምኜ ምከሩት፣ በጉልበት አግዙት፣ በምክር ደግፉት። ልጄን አደራ መስጠቴ ከልጄ ጋር ኢትዮጵያን አደራ ጠብቁ ማለቴ ነው። ...የደጊቱ አገራችን ኢትዮጵያ አምላክ ይገዛችሁ፡ ይጠብቃችሁ። ከዚህ ቃል የወጣ በሰማይም ነፍሱ፣ በምድርም ሥጋው ልጅ እስከ ልጅ ልጁ የተረገመ ይሁን፣ የኢትዮጵያ ውቃቢ ያጥፋው፣ እኔም ሳለሁ ከፍቃዴ የወጣ ረግሜዋለሁ።”

በግዜው የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳሳት አቡነ ማቴዎስም የአጼ ምንሊክ አደራ ለማይቀበሉ ሁሉ አወጋዙ፦ “ልጆቼ የኢትዮጵያ ሰዎች፣ መኳንንቱም ሠራዊቱም፣ ባላገሩም፣ ወታደሩም፣ የኔን ያባታችሁን ቃል ስሙ...የእግዚአብሔር ወዳጅ ዳግማዊ ምኒልክ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ከልጅነትዎ ጀምሮው እስካሁን ድረስ በትጋትና በመቻል በቸርነትም ያቀኑትን የኢትዮጵያ መንግሥት ለሰጡዋቸው ልጅ ከዕረፍትም በኃላ ፈቃዳችሁና ፈቃዱ አንድ ሆኖ እንድትታዘዙት ይሁን።”

እንደገና በጥቅምት 20 1902 አጼ ምንሊክ ፊርማቸውና ማህተማቸው ያለበት ሁለተኛ አዋጅ በነጋሪት አስታወቁ፦ “አሁንም ከዚህ ቀደም እንዳስታወቅኋችሁ፣ የእግዚአብሔር ፈቃዱ ቢሆን ያልጋየ ወራሽ ልጄ የወይዘሮ ሸዋረጋ ልጅ ከራስ ሚካኤል የተወለደው ኢያሱ ነውና፣ ራስ ቢትወደድ ተሰማን ሞግዚት አድርጌ ሰጥቻችኋለሁ። አልጋየን የሚጠብቅ እሱ ነው።”

አጼ ምንሊክ በታሕሳስ 3 1906 ዓ.ም. ዓረፉ፣ ስለማለፋቸው ግን በይፋ እንዳይገለጽ አቤቶ ኢያሱ ትእዛዝ ስላስተላለፉ የኢትዮጵያ ሕዝብ አልሰማም ነበር። ይኸን ውሳኔ ለማድረግ ያስገደዳቸው ምክንያትም በኢትዮጵያ ጸጥታ እንዳይደፈርስና የክፍላተ ሃገር ገዢዎች እንዳይሸፍቱ በመስጋት ነው የሚሉ ጸሓፊዎች ሲኖሩ፣ አንዳንድ በግዜው የነበሩትን ባለሥልጣናት ግን ልጅ ኢያሱ ለታላቁ መሪ ለአጼ ምንሊክ ክብር በመንሳት አስፈላጊውን የቤተ መንግሥት ስነ ስርዓት ፍትሓትና ቀብር ማድረግ ስላልፈለጉ ነው የሚል ትርጓሜ የሰጡትም አሉ።

ያም ሆኖ ይህ አጼ ምንሊክ ከሞቱ በኋላ ምንስትሮቹ ለአቤቶ እያሱን ያቀረቡትን ምክር አቶ ጉበዜ በገጽ 57 ውስጥ በእንዲህ መልክ አስቀምጠውታል፦ “በ1906 ዓ.ም. ሚኒስትሮችና መኳንንቶች በቆይታ ተመካክረው ለአቤቶ ኢያሱ የምክር ቃል አቀረቡ ሲባል ተሰማ። የምክሩ ቃል ‘ጃንሆይ አጼ ምንሊክ በሕይወታቸው ሳሉ አልጋወራሼ ኢያሱ ነው ብለው አስታወቁን። አሁን እሳቸው ዓረፉ። እንግዲህ ምን እስኪሆን እንጠብቃለን፣ የዘውድ በዓልዎ የሚደረግበትን ቀን እንወስንና ዘውድ ደፍተው በአባትዎ መንበረ ዳዊት ይቀመጡልን’ የሚል ነው።

“አቤቶ ኢያሱም ምክራችሁ መልካም ነው፣ እኔም ሳላስብበት አልቀረሁም። ነገር ግን አባቴን ራስ ሚካኤልን በፊት ንጉሥ አሰኝቼ፣ በኋላ ንጉሠ ነገሥት መሆን ይገባኛል” ብለው መለሱላቸው። “ከዚህም ጋር አያይዘው ፈረሴ ከምጽዋ ውኃ ሳይጠጣ ዘውድ ጭኜ ንጉሠ ነገሥት አልባልም” እያሉ መቆየታቸው የሚታወስ ነው።

ነገር ግን ልጅ ኢያሱ በገዛ ፈቃዳቸው ‘ንጉሠ ነገሥት’ ባይባሉም ቅሉ በክፍላተ ሃገር እየተዘዋወሩ ሕዝቡን ለማሰተባበር ጥረት አድርገዋል። ይህ በእንዲህ እያለ ግን በሞግዚትነት ያገለግሏቸው የነበሩትን ራስ ቢትወደድ ተሰማ በምያዝያ 3 1913 ስለሞቱ በአጼ ምንሊክ ዙርያ የነበሩትን አንዳንድ ባለሥልጣናት በአቤቶ ላይ ዘመቻ ማካሄድ ጀመሩ። የዚሁ ዘመቻ ዓይነተኛ ምሳሌ በአቶ ተክለሓዋርያት የተሰነዘረውን ሆኖ በአቶ ዘውዴ መጻሓፍ ውስጥ የተጠቀሰውን ነው፦ “አባ ጤና ኢያሱ በጉዙአቸውና በጉብኝታቸው ወቅት የሚፈጽሙት እጅግ የረከሰ የብልግና ጠባይ

ከመጠን በላይ አሳዘናቸው። ተክለሓዋርያት በማስታወሻቸው የገለጹት…ልጅ እያሱ እንደ ዓረቦቹ ጠምጥመው፡ ዓረቦቹ ግራና ቀኝ በሰልፍ ሆኖው፡ እሳቸው ማህል ግድግዳውን ተደግፈው፡ በሁለቱም ጉንጮቻቸው ጫት ጠቅጥቀው ስያመነዥኩ ያገኟቸዋል። አባ ጤና ዓይኖቻቸው ደፍርሰው ሲቅበጠበጡ፣ በአለባበሳቸውና በአኳኋናቸው፡ የኢትዮጵያ የክርስትያኖች ንጉሥ መሆናቸው ቀረና፡ የእስላም ሡልጣን ሆኑ ወይ? የምያሰኝ ሁኔታ ይታይባቸው ነበር።” (ገጽ 237)

የዚሁ የአቶ ተክለሓዋርያት ተቃራኒ የሆነውን ደግሞ በአቶ ጐበዜ መጽሓፍ ወስጥ የቀረበውን እንዳለ ማቅራብ አስፋለጊ ስለሆነ ይኸውና፦ “የልጅ ኢያሱ ቀዳሚ ዓላማቸውና ምኞታቸው ኢትዮጵያውያን ሁሉ በጐሣና በሃይማኖት ሳይከፋፈሉና እስላም ክርስትያን በመባባል ሳይነቃቀፉ፡ ማለት ሆድና ጀርባ ሳይሆኑ በእኩልነት አንድነታቸውን አስተባብረውና አጠናክረው የኢትዮጵያን ልዓላዊነት ለማስከበርና በቅኝ ገዥዎች የተያዙትን ጥንታዊ ጠረፎችዋን ነጻ ለማውጣት ነበር። ደጋግመው ‘ፈረሴ ከምጥዋ ውሃ ሳይጠጣ ዘውድ ጭኜ ንጉሠ ነገሥት አልባልም” እያሉ በግልጥ ይናገሩ ነበር ይባላል።

አጀማመራቸው ሁሉ፣ በማያጠራጥር ሁኔታ በሀገር ፍቅር የተሞላና ብሩህ ሕሊና ያላቸው ሰው ነበሩ። ነገር ግን፣ ስለዘመኑ የፖለቲካ ዘዴና የተለባብሶ መኖር ጉዳይ፡ ትልማቸው ጥልቀትና ብስለት አልነበረውም።

ከአቤቶ የእልፍኝ አስከሮች አንዱ በቀለ አበሻ የሚባሉት የሚከተለውን አጫውተውኛል። ‘በ1907 ዓ.ም. ጌታየ አቤቶ ኢያሱ በእንግሊዝ ሌጋስዮን ሻይ ተጋብዘው ስለነበር፡ ከእልፍኝ አሽከሮች ጥቂቶቻችን አጅበናቸው ሔደን ነበር። የየሊጋስዮኖች ሚኒስትሮችም እንዲሁ ተጋበዘው ነበር። በዚሁ የሻይ ግብዣ ላይ ጌታየ ስም ሳይጠሩ፣ ‘እናንተም ጠረፎቼን ለቃችሁልኝ በየአገራችሁ እንድትኖሩና እኔም የአገሬን ጠረፎች ዳር ድንበር አስከብሬ በሰላም እንድኖር እመኛለሁ’ ብለው በግልጽ ተናገሩ።’

እንዲህ ያለው ብስለት የሌለው ግልጥ አነጋገርም ሦስቱን ተጎራባች ቅኝ ገዥዎች ከባላንጣዎቻቸውና ከቤተ ክህነት ሰዎች ጋር አስተባብሮ መንግሥታቸውን ለመሰርሰር አስቻላቸው። ከዚህም በቀር የንጉሥ ሚካኤል በሰሜኑ ክፍላተ ሃገር ላይ መንገሥና የልጅ ኢያሱ የፖለቲካ አመራር አቅጣጫ የሸዋን መኳንንት ከጥርጣሬ ላይ መጣሉ አልቀረም። ሆኖም ሚኒስትሮቹ ልጅ ኢያሱን በስም ብቻ ሊቀ መንበራቸው አድርገው የመንግሥቱን ሥራ በኅብረት በማከናወን ከኃላፊነት ገላግለዋቸው ነበር። ልጅ ኢያሱም በዕድሜ ገና ወጣት ከመሆናቸው የተነሣ የማስተዳደር ተግባር አሰልቺና አድካሚ ስለሆነባቸው፣ በዚሁ ፈንታ ወደየጠረፉ እየተዘዋወሩ ስለአንድነት ጉዳይ ለሕዝቡ ያስረዱና በኃይልም ይሰብኩ ነበር ይባላል። ነቃፊዎቻቸው ግን ከጠረፍ እስከጠረፍ አዘውትረው የሚዘዋወሩበት ምክንያት ከቆነጃጅት ጋር ለመዳራት ነው፣ አጃቢዎቻቸውም ተራ ሰዎች አጨብጫቢዎች፣ እበላባዮችና አድርባዮች ናቸው በማለት ያጥላሉዋቸው ነበር.” (ገጽ 65-66)

የልጅ ኢያሱን ተቃዋሚ ኃይሎች ዘመቻቸውን በማጦፍ አቤቶ የመንግሥት ኃላፊነታቸውን በመዘንጋት ብቻ ሳይሆን የክርስትና ኃይማኖታቸውን በመተው የእስልምና ኃይማኖት ተከታይ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ልዩ ልዩ ፕሮፓጋንዳና

ቅስቀሳ አካሀዷል። የስም የማጥፋቱ ጉዳይ ዋና ዓላማ ግን፣ ቆየት ብለን እንደምናየው ሁሉ፣ በመንግሥት ለውጥ ላይ ያተኰረ ነው።

ብዙ በግዜው የነበሩ ጸሓፊዎች፡ ለምሳሌ እንደ ሓለቃ ገበረእግዚአብሔር ኤልያስ የመሳሰሉትን ግን ልጅ ኢያሱ ሕዝቡን በማሰተባበር ረገድ ከፍተኛ ጥረት ከማድረጋቸውም በላይ እስላሙና ክርስትያኑም በእኩልነት ያዩ እንደነበር ነው የመዘገቡት። አቶ ጉበዜ በመጽሓፋቸው እንዳመለከቱትም ልጅ ኢያሱ አነስተኛ ከተሞችን እንደቆረቆሩ፣ በ1903 ዓ.ም. በአዲስ አበባ የቀጨኔ መድኃኔ ዓለም ቤተክርስትያን እንደሰሩ፣ በ1904 ዓ.ም. ጥርግያ መንገዶችን እንደሰሩ፣ 'ድሃ ተበደለ፡ ፍርድ ተጓደለ' ለሚለው አቤት ባይ ይሰሙና ወንጀለኛውን ይቀጡ እንደነበር፣ ኋላቀር ያሰራር ልምድም ለመቀየር አምስት ሕጎች እንዳወጡ ወዘተ የልጅ ኢያሱን አካሄድና አስተዳደር ከሞላጎደል ያንጸባርቃል።

ልጅ ኢያሱ እስላም ሆነዋል ብለው ስማቸውን የምያጠፏቸው ግለሰቦች ወይም የአድማ ስብስቦች ለውንጀላው ምንም ዓይነት ማረጋገጫ አላቀረቡም። በአንጻሩ አቶ ጉበዜ እንዳመለከቱት፣ "በግንቦት 15 ቀን 1905 ዓ.ም. ከደሴ ተነሥተው በቀጥታ ወደ ደብረ ሊባኖስ ከተጓዙ በኋላ የአቡነ ተክለኃይማኖትን በዓል አክብረው ለገዳሙ መርጃና ለካህናቱም ሰፊ ችሮታ ከማድረጋቸው በላይ ከየቦታው ለመጡት መኳንንትና ሠራዊት፣ አለቆችና ካህናት ሙሉ ግብር አበሉ።" (ገጽ 70)

አቶ ዘውዴ እንዳስቀመጡት ከሆነ ግን ልጅ ኢያሱ የኢትዮጵያን ሕዝብ በማስተባበር በኃይማኖትም ረገድም ልዩነት እንዳይኖር ጥረት ከማድረግ ይልቅ ኢትዮጵያን ለማስለምና ሕዝቡን እርስ በራሱ ለማጋጨት እቅድ እንደነበራቸው ነው። በዚሁ መልክም ሰፍሯል፦ "ሸዋ ተሰብስባ ብትዶልት ምን ፍሬ ትሰጣለች? ሸዋ ዙርያዋን የከበባት እስላም ነው። እንድያውም ቆይ ታያለህ! ኢትዮጵያን አሰልማታለሁ።ይኸንን ያላደርግኩ እንደሆነ እኔ ኢያሱ አይደለሁም...ብለው ሲፎክሩ ተክለሓዋርያት ደንግጠው ከፊታቸው ዘወር አሉ።" (ገጽ 240)

በተጨማሪም አቶ ዘውዴ እንደመዘገቡት ከሆነ ልጅ ኢያሱ እንዲህ ብለው ተናገሩ፦

"ሸዋ ቢዶልት የት ሊደርስ ይችላል?<br>
በአንድ ጊዜ እደመሰሰዋለሁ...<br>
እኔ ኢያሱ፡ ሸዋን ልሸናብህ ብለው እንኳ፣<br>
አፉን ከፍቶ እንደሚቀበለኝ የታወቀ ነው<br>
...ከፈለግኩ ደግሞ፡ የጉራጌውንና<br>
የጋላውን ባላባት አንድ ምልክት<br>
ብሰጠው አዲስ አበባን በአንድ አፍታ<br>
ሊያቃጥላት ይችላል..."

በአቶ ጉበዜ እንደተገለጸው ከሆነ ደግሞ፣ ልጅ ኢያሱ እንኳንስ የኢትዮጵያን ሕዝብ በጎሳ ለማጋጨት ይቅርና አስተሳሰቡም እንዳልነበራቸው ነው። እንድያውም በኃይማኖትና ጎሳ ልዩነት ሳይደረግ በኢትዮጵያዊነት ስሜት ይገፋፉ እደነበርና ከዘም አልፎ ተርፎ ኤርትራን ለማስመለስ ግዙፍ እቅድ እንደነበራቸው ነው። አቤቶ

ኢያሱ ኤርትራን ለማስመለስ የነበራቸውን ምኞትና ንድፍ በአቶ ጕበዜ መጽሐፍ ውስጥ በሚከተለው ተጠናክሮ ቀርቧል፦

“በ 1907 ዓ.ም. በሚያዝያ፣ ግንቦትና ሐምሌ ወራት ‘ከእንግዲህ ወዲህ የዮሐንስን ምድር ኤርትራን ከመሞቴ በፊት ማስመለስ አለብኝ። ሹማምንትና ወታደሮች ሆይ፣ ፈረሶቻችሁና በቅሎቻችሁን ጫኑ፣ ቀልቧቸውም፣ ስንቃችሁንም ሰንቁ’ እያሉ በግልጥ ይናገሩ ነበር።

የመጀመርያው የዓለም ጦርነት በተቀሰቀሰ ጊዜ ልጅ ኢያሱ የክተት አዋጅ በመላ ኢትዮጵያ ዓወጁ።

ጳጉሜ 5 1907 ዓ.ም. እንግሊዝ፡ ፈረንሳይና ጣልያን ስለዚህ አዋጅ ማብራርያ እንዲሰጣቸው የኢትዮጵያን መንግሥት በይፋ ጠየቁ።

ልጅ ኢያሱም ስለ ዓዋጁ ከኃያላኑ በቀረበላቸው ጥያቄ አልደነገጡም፣ ዋጋም አልሰጡትም ነበር።

ነገር ግን የመጀመርያው የዓለም ጦርነት በተቀጣጠለበት ጊዜ በኃያላኑ የነበረውን ውጥረት ለልጅ ኢያሱ በኢጣልያ ቅኝ ግዛት በኤርትራ ላይ አደጋ ለመጣል አመቺ ጊዜ የፈጠረላቸው መስሎ ታየ። ስለዚሁ ዘመቻ እቅድ ለመንደፍ ልጅ ኢያሱ በ1907 ዓ.ም. መጀመርያ ወራት ላይ ወደ ደሴ ሔደው ከአባታቸው ጋር ሲመካከሩ ከረሙ። ጥር 27 ቀን 1907 ዓ.ም. ከጣልያን የሚሥጢር ሠራተኛ የተገኘ መረጀም፦

‘ግዙፍ የሆነ ራሳቸው ልጅ ኢያሱ የሚሳተፉበት የኢትዮጵያ ሠራዊት እንደሚከተለው በሦስት አቅጣጫዎች በኤርትራ ላይ ሊዘምት ነው’ የሚል ነበር።

አራት ጀርመናውያን አማካሪዎች ባሉበት የተነደፈው ዕቅድም

1ኛ) በራስ ይመር የሚመራ ከሠላሳ እስከ ዐርባ ሺህ ያህል የታጠቀ ጦር አዲግራትን አቋርጦ በመዝመት የወረራ ሙከራ እንዲያደርግና የጠለት ኃይል ሠፈሩን ለቆ እንዲያፈገፍግ ማድረግ።

2ኛ) አንድ ሌላ ኃይል ደግሞ በሁለት አቅጣጫ ተሠልፎ ከዓድዋ ወደ አሥመራ እንዲንቀሳቀስ ፦

ሀ) በዋግሹም ገብረ ሕይወት የሚመራ ስድሳ ሺ ጦር የተሰለፈበት ደግሞ የመረብን ወንዝ ተከትሎ ከሰንዓፌ ወደ አዲግራት እንዲንቀሳቀስ፣

ለ) አንድ ሌላ በልጅ ኢያሱ በራሳቸው የሚመራ አንድ መቶ ሰማንያ ሺህ ሰዎችን ያቀፈ ሠራዊት መራጉዝን እንዲሻገርና በባረንቱና በከረን አቋርጦ የሚጓዘውን ስድሳ ሺ የራስ ወልደ ጊዮርጊስን ጦር እንድያግዝ፣ ከዚህም በኋላኛው የአንደኛው ክፍል ኃይል አሥመራ ሊጓዝና ከሁለተኛው ክፍል ጋር ከረን ላይ ተገናኝቶ ወደ ምጥዋ እንዲጓዝ ነበር።

3ኛ) አንድ ሦስተኛ ከአፋር ጕሣ የተመለመለ ዐርባ ሺ ሠራዊት ደግሞ ከዙላ ተንቀሳቅሶ ምስራቃዊ ኤርትራን እንዲከብ፣ መስከረም 2 1908 ዓ.ም. ይፋ የወጣው ሁለተኛ ወታደራዊ መረጃ ደግሞ ‘በአራት ጀኔራሎች የሚመራ የታጠቀ የኢትዮጵያ ሠራዊት በኢጣልያ ቅኝ ግዛት ላይ አደጋ ለመጣል በሚከተሉት አራት አቅጣጫዎች በጉዞ ላይ ነው’ የሚል ነው። እርሱም፦

ሀ) በራስ ወልደጊዮርጊስ የሚመራ ኃይል ወልቃይትን አቋርጦ ወደ ባረንቱ እንዲዘምት፣

ለ) በራስ ደምስ የሚመራው ኃይል በአዲኳላ አድርጎ ወደ አዲዑግሪ እንዲንቀሳቀስ፣

ሐ) በልጅ ኢ.ያሱ በራሳቸው የሚመራው ኃይል በጸሮና በኩል ወደ ኩቲትና (ኩዓቲት) ሰገነይቲ እንዲዘምት፣

መ) በንጉሥ ሚካኤል የሚመራው ኃይል ደግሞ በአዲግራት በኩል ወደ ሽሜጃናና ሰንዓፌ እንዲንቀሳቀስ ነበር። (ገጽ 80-81)

እላይ የተጠቀሰውን የልጅ ኢ.ያሱ ኤርትራን ለማስመለስ ያወጡትን ታላቅ የወታደራዊ ንድፍ የኢጣልያን መንግስት በጣም ሲረብሸው የእንግሊዝና የፈረንሳይ መንግስታት ደግሞ እጅግ እንዳሳሰባቸውና ስለጉዳዩ በግልጽ መናገር እንደጀመሩ የታሪክ ሰዎች መዝግበውታል። ከዚህ በኋላ በልጅ ኢ.ያሱ ላይ ከውስጥ ብቻ ሳይሆን ከባዕድ መንግስታትም ጭምር ተቃውሞና ሴራ መካሄድ ጀመረ።

አሁን በልጅ ኢ.ያሱ ላይ በቅኝ ገገርዎች ኃያላንና በሸዋ መኳንንት ቅንጅት የሚካሄደውን ዘመቻ በይፋ መውጣት ጀመረ። በአቶ ዘውዴ እንደተገለጸው በዘልማድ በሰምና ወርቅ መልክ የሚቀርበውን የግዜውን ፖለቲካ የሚያንጸባርቅ ዘይቤ በዚሁ መልክ ቀረበ፦

ሸዋ መከረ ኢ.ያሱን ሻረ
ስትፈትል አዝየ፡ ስትፈጭም አዝየ
ጀርባየ ተላጠና ውረድ ማሙዬ (ገጽ 245)

ጣልያኖች የአንደኛ ዓለም ጦርነት ከመገባደዱ በፊት፡ ልጅ ኢ.ያሱን አስመልክቶ ለእንግሊዞች የላኩትን የምሥጢር ሰነድ ደግሞ እንዲህ ያነባል፦ “በሃገር ውስጥ በልጅ ኢ.ያሱ ላይ ከተነሱባቸው ጠላቶቻቸው መካከል ደጃዝማች ተፈሪ መኰንን፣ እጨጌ ወልደጊዮርጊስ፣ ፊተውራሪ ሃብተጊዮርጊስና ደጃዝማች ይገዙ በሃብቴ ናቸው” ይላል (አቶ ጕበዜ ገጽ 82)

ልጅ ኢ.ያሱ ስለባዕድና አገር ውስጥ ስለሚካሄደው ሴራ ብያውቁም ቅሉ የተለመወደውን አገር የማሰተባበርን ጉዳይ ለመቀጠል በ1908 ዓ.ም. እንደገና ወደ ሐረር ተጓዙ። “በሃይማኖትና በጎሣ ብንለያይም የአንዲት ኢ.ትዮጵያ ልጆች ስለሆን፡ በብሔራዊ ስሜትና ፍላጎት አንጻር እንድንተባበርና አንድነታችን እንዲጠነክር እመኛለሁ፡ ከሌሎች ኢ.ትዮጵያውያን ወንደሞቻችሁ ጐን በአንድነት ተሰልፋችሁ በመቆም አገራችሁና ጠረፎችዋ ይጠበቃሉ” በማለት ለህዘቡ እንደገና አስታወቁ። ከዚህም አልፎ ልጅ ኢ.ያሱ ኢ.ትዮጵያ በራስ ገዝ አስተዳደር የምትተዳደርበት መንገድ ቀይሰው ነበር፣ እስላሙና ክርስትያኑ ባንድነት መኖር እንዳለባቸው የሚል መርሆአቸውም ቀጠሉበት። ጠላቶቻቸውን እንደሚነዙት ወሬ ሳይሆን ደግሞ አብያተ ክርስትያን ከመስራትም አልተቆጠቡም።

ልጅ ኢ.ያሱ ድሬዳዋ አከባቢ. በቆዩበት ግዜ ደጋግመው ስለ ኢ.ትዮጵያ ነጻነትና ልዑላዊነት ይሰብኩ ነበር፣ እሳቸው ባሉበት በተደረገው ሰልፍ ለሰልፈኞቹ ሰንደቅ ዓላማውን ሲያስረክቡ “ሃይማኖት የግል ነው፣ ኢ.ትዮጵያ ግን የጋራችን ናትና፣ እኔም

ሃይማኖታችሁን አከብራለሁ። እናንተም የሃገራችሁን ድንበር ጠብቁ” ብለው መከሯቸው። (አቶ ጐበዜ ገጽ 95)

በጣም የሚገርመው ግን ብዙ ኢትዮጵያዊ ማለትም በአጼ ኃይለሥላሴ ዘመነ መንግሥት የተወለደና ያደገ ‘ኃይማኖት የግል ነው፣ አገር የጋራ ናት’ የሚለው መፈክር የልጅ ኢያሱ ሳይሆን የአጼ ኃይላሥላሴ መሆኑን ነው የምያውቀው። እንዴትስ ብሎ ይወቀው? ቀደም ብዬ እንደተቀስኩት ታሪክ በመጠኑም ቢሆን በባለሥልጣን ነውና የሚጻፈው ቀጥለን እንደምናየው አቤቶ ኢያሱ ተሽረው ደጃዝማች ተፈሪ በትረ ስልጣኑን ስለያዙት መፈክሩም ሳይቀር የራሳቸው ንብረት ሆነ። የሆኖ ሆኖ ግን አሁንም ቢሆንም፡ እኔም በግሌ ያጋጠመኝ፡ ምሁራን ነን ባዮች የውሸት ፖለቲከኞች፡ ጽንሰ-ሓሳብ፣ ዘይቤ፣ መርሓ-ግብር ከሌላ ጸሓፊ ይሰርቁና እነሱ እንጻፈለቁት አድርገው ያስቀምጡታል።

እስካሁን ድረስ እንዳየነው የልጅ ኢያሱ አርቆ አስተዋይነትና አገር ወዳድነት የምያጠያይቅ አይደለም። ነገር ግን የፖለቲካ ውስብስብነት በመገንዘብ ረገድ የተካኑ እንዳልሆኑ ማእከላዊ መንግስትን ትተው ዳር ዳሩን ብቻ ላይ ማተኰራቸው በገሃድ የምያሳይ ነው። በየትም ዓለም፡ የትም ሕብረተሰብ ግለሰብ ይሁን ስበስብ የማእከላይ መንግሥት መዋቅሮችን ካልተቆጣጠረ የመንግሥት አስተዳደርን በሚፈልገው እቅድ መሰረት ሊያንቀሳቅስ አይችልም። በተጨማሪ ልጅ ኢያሱ ያልተገነዙበት ነገር ቢኖር ‘የናቁት ያስረግዛል’ የሚለውን ያበው አነጋገር ነው። እነ ደጃዝማች ተፈሪን፡ እነ እጨጌ ወልደጊዮርጊስን፡ እነ ፊተውራሪ ሃበተጊዮርጊሰ አባ መቻልን መናቅ የፖለቲካ የዋህነትን ነው የምያንጸባርቀው። ለነገሩ የአድማው ዋና ተዋንያን እጨጌ ወልደጊዮርጊስና ፊተውራሪ ሃብተጊዮርጊስ በአንደኛ ደረጃ ሲታዩ፣ እነ ሊጋባ በየነ አባ ሰበስብ እና እነ ደጃዝማች ኃይለማርያም ለማ ደግሞ የሁለተኛ ደረጃ ሚና ነበር የተጫወቱት። ደጃዝማች ተፈሪ መኰንን ግን ብልህና ረቂቅ ስለነበሩ እንኳንስ በአድማው ላይ የተጫወቱት ሚና በይፋ ለማስታውቅ፡ እንድያውም በነገሩ እንደሌሉበት ነበር ያስወሩት።

ከጳጉሜ 2 1908 እስከ ነሓሴ 1908 የአድማው ሴራ እየሰፋ መጣ። በመስከረም 16 1909 ደግሞ ልጅ ኢያሱን ከሥልጣን ለማውረድ አዲስ አበባ ውስጥ ጉበዔ ተካሄደ። በዚሁም ጉባዔ ወይዘሮ ዘውዲቱን ንግሥተ ነገሥታት ፣ ራስ ተፈሪ ደግሞ ባለሙሉ ሥልጣን አልጋወራሽ እንዲሆኑ ተወሰነ። በውስኔውም መሰረት በመስከረም 21 1909 የንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ቅብዓ-ነገሥትነት ተካሄደ። የጉባዔው ውሳኔና የልጅ ኢያሱ መሻር ግን በርካታ የኢትዮጵያ መኳንንት ተቃውሞውታል፦ የጎጃሙ ራስ ኃይሉ ተክለኃይማኖት፣ የትግራዩ ደጃዝማች ካሣ ስዩም (የአክሱም፡ የዓድዋና ሽረ ገዢ የነበሩት)፣ የልጅ ኢያሱ ጠቅላይ ሚንስተር የነበሩት ቢትወደድ ኃይለጊዮርጊስ ወልደሚካኤል እንደ ምሳሌ መጥቀስ ይቻላል። ሌሎች ብዙ የተጠረጠሩ መኳንንት ደግሞ ከልጅ ኢያሱ ጋር ግንኙት አላችሁ ወይም ለአዲሱ መንግሥት እውቅና አልሰጣችሁም በሚል ክስ የተጋዙ አሉ።

ንግሥት ዘውዲቱ በአባታቸው መንበረ-ዳዊት ቢቀመጡም፣ ልዑል ራስ ተፈሪ ደግሞ አልጋወራሽ ብለው ቢሰየሙም፡ ልጅ ኢያሱን በቍጥጥር ስር ካላዋሉ ግን ሰላም ልያገኙ እንደማይችሉ ስለተገነዘቡት በአቤቶ ላይ የስነ-ልቦና ዘመቻ ብቻ ሳይሆን

የወታደራዊ ዘመቻም ጭምር ማካሄድ እንደነበረባቸው በቅጡ አውቀዉት ነበር። ስለሆነም ራስ ተፈሪ ወደ ሓረር ሠራዊት በመላክ ልጅ ኢያሱ የሚያዙበትና የሚታሰሩበት ትእዛዝ አስተላለፉ፣ አቤቶ ግን ምንም እንኳ በዚሁ በቀውጢ ቀን ፈረንሳዮች ድጋፍ ልያደርጉላቸው እንደሚፈልጉ በሚስጢር መልእክት ቢሉኩላቸውም፡ አሻፈረኝ በማለት በአንኮበር አድርገው ወደ ደሴ ወደ አባታቸው ለመሄድና ከዛው ኃይላቸውን በማጠናከር ለመዋጋት ወሰኑ። ነገር ግን ከአባታቸው ከንጉሥ ሚካኤል ጋር ከመቀላቀላቸው በፊት የሰገሌ ጦርነት በጥቅምት 17 1909 ዓ.ም. ተካሂዶ የራስ ተፈሪ ኃይሎች ድል ስላደረጉና አባታቸውም ምርኮኛ ስለሆኑ አማራጩ ከጠላት ኃይል መሸሽና ማምለጥ ብቻ ነበር።

የልጅ ኢያሱ መኰብለል ግን የራስ ተፈሪ አዲሱን መንግሥት ፋታ ስለነሳው ልዑል አልጋወራሹ በግዜው በነበረው የእንግሊዝ ባለ ሙሉ ስልጣን ሚኒስተር ለ ዊልፈርድ ተሲግር የሚከተለውን ጻፉለት፦ "ልጅ ኢያሱ አያታቸውን የጣሉባቸውን አደራ ስተው የኢትዮጵያን ሕዝብ በሃይማኖት እርስ በርስ ለማስጨረስና የአገሪቱንም አንድነት ለማፍረስ በመነሣታቸው እሳቸው ተሽረው ንግሥት ዘውዲቱና እኔ ስንመረጥ ብዙ ችግሮችና ብዙ መሰናክሎች እንደሚገጥሙን እናውቅ ነበር...ለአገራችን ሰላምና ፀጥታ ጠንቅ የሆኑብን ልጅ ኢያሱ ስላልተያዙ ምን ያህል ችግር እንደሆነብን እርስዎ ደህና አድርገው የሚያወቁት ነው።" (አቶ ዘውዴ ገጽ 343)

ራስ ተፈሪ የእንግሊዞች መተባበርና እርዳታ ባይሳካላቸውም በአንዳንድ ኢትዮጵያውያን መኳንንት ተባባሪነት ልጅ ኢያሱን ከቍጥጥራቸው ስር ለማዋል በቅተዋል። ልጅ ኢያሱ አንዴ በአውሳ በረሃ፡ ሌላ ግዜ በመቅደላ ምሽግ ሲንገላቱ አዲሱ መንግሥትም እየተደላደለ ስለመጣ ተቃውሞ ያሳዩትን እንደ ራሰ ኃይሉ ተክለኃይማኖት ሳይቀሩ ልጅ ኢያሱን አድነው እንደምይዙ አስታወቁ።

ልጅ ኢያሱ ከመቅደላ አፈግፍገው ወደ ትግራይ ካመሩ በኃላ ወሬው አዲስ አበባ አከባቢ ስለደረሰ ልዑል ራስ ተፈሪ ከትግራይ ተይዘው የሚመጡበት መንገድ ዘዴ ፈለጉ። ይህ በእንዲህ እንዳለ ሁለት የትግራይ መኳንንት ማለትም ራስ ስዩም መንገሻና ራስ ጉግሳ አርኣያ በልጅ ኢያሱ ጉዳይ ላይ የተለያየ አቋም ነበራቸው። አቶ ዘውዴ በመጽሓፋቸው እንደገለጹት የሁለቱ መኳንንት አቋም ከዚሁ በሚቀጥለው ሰፍሯል፦

"ልጅ ኢያሱ በየበረሃው ሲሰቃዩ ከኖሩ በኋላ፡ እህታቸውና ወንድማቸው ቤት ደርሰው አድኑኝ ብለው ሲማጸኑ፡ በሰብዓዊ መንፈስ ምሕረት ለማስገኘት ጥረት ይደረጋል እንጂ እጃቸውን ይዞ መስጠት የአረመኔ ሥራ ነው" (የራስ ስዩም {መንገሻ} አስተያየት)

"ኢትዮጵያን ለማስለም የተነሣውን መሪ ጳጳስ ገዝቶታል፣ ሕዝብ አልቅሶበታል። ስለዚህ ወንጀለኛውን እጁን ይገፍ ባስረክብ፣ እግዚአብሔር አይጣላኝም፡ ሕዝብም አይታዘበኝም" (ራስ ጉግሣ አርኣያ) (አቶ ዘውዴ ገጽ 393 ና ገጽ 401)

ራስ ጉግሣ ጳጳሱ ልጅ ኢያሱን እንዳወገዙ አድርገው ያቀረቡት ግን ትክክል አይደለም። በእርግጥ በነበረው የወቅቱ ፖለቲካ ብዙ ውዥንብሮች ተፈጥረው ስለነበሩ ምልአተ ሕዝቡና ባለሥልጣናት ተደናግረው ነበር ማለት ይቻላል። ከላይ የተጠቀሱትን ሰዎች በልጅ ኢያሱ ላይ ሴራ ከጠነሰሱ በኋላ ጳጳሱን የአጼ ምንሊክ አልጋወራሽን እንድያወግዙ ጠየቋቸው። ጳጳሱ ግን በማመንታት መጀመርያ ሁኔታውን ላጣራ፣ ደግመውም ለአድመኞቹ እኔው ራሴ ላሰታርቃችሁ በማለት ተማለዷቸው። አድመኞቹ ግን የጳጳሱ ሓሳብ ከመጤፍም ሳይቆጥሩ እንድያወግዙ ብቻ ነበር የጠየቋቸው። ከዛም አልፎ ተርፎ አድመኞቹ ጳጳሱን ማስፈራራት ጀመሩ። አንዳንዱ ‘ማውገዝ አለብዎት፣ ባሁኑ ግዜ ለልጅ ኢያሱ ምክር ማለት ዋጋ የሌለው ዓላማ ነው’ ሲሉ አንዳንዱ ደግሞ ‘ማውገዝ ያልፈለጉበት ምክንያት የራስዎ አገር ንጉሥ የመሓመድ ተከታይ ስለሆኑ ነው’ ያሉም ነበሩ። ‘የራስዎ አገር ንጉሥ…’ ያሉበት ምክንያትም አቡነ ማቴዎስ (ጳጳሱ) የግብጽ ተወላጅ ስለሆኑ ነው። ከዛም አልፎ ተርፎ አንዳንዶቹ አካኪ ዘራፍ በማለት የኃይል ምልክት (ጠብ-መንጃ) ስለሰነዘሩ ጳጳሱ ሳይወዱ ልጅ ኢያሱን አውግዘዋል። ከልባቸው ያመኑበት ነገር ግን አልነበረም። ይኸንን ጉዳይ ራስ ጉግሣ ወይ አልተገነዘቡትም ነበር ወይም ደግሞ በሥልጣኑ ሽኩቻና ግርግር ውስጥ ተሳታፊ ለመሆን ያደረጉት ጥረት ብቻ ሊሆን ይችላል። ግራም ነፈሰ ቀኝ በራስ ጉግሣ አማካኝነት ልጅ ኢያሱ ትግራይ ውስጥ ተያዙ።

“ጥር 20 1913 ዓ.ም. አንድ ጠቋሚ፣ ራስ ጉግሣ አርአያን ከጥቂት ሰዎች ጋርና በዓድዋ ግዛት የልዑል ራስ ተፈሪ እንደራሴ የነበሩትን ልጅ ደስታ ዳምጠው /በኋላ ራስ/ እየመሩ ከዓድዋ ወደ ደቡብ ተጉዘው በሰለዋ ቀበሌ የምትገኘውን የግብጻውያን ገዳም ከበው ልጅ ኢያሱንና ጥቂት ተከታዮቻቸውን ያዙ። ልጅ ኢያሱንም በሰላም ለራስ ጉግሣ አስረከቡ። ራስ ጉግሣም የዓፄ ምኒልክን የልጅ ልጅ ጫማ ስመው ልዩ ጠባቅያቸው እንደሚሆኑ ገለጡላቸው። ማራኪና ተማራኪ ከዚያ ተነሥተው ጉዞዋቸውን በመቀጠል ጥር 23 ቀን ቀትር ላይ ማይጨው ደረሱ። ለልጅ ኢያሱም ውሃ ቀርቦላቸው ሰውነታቸውን ታጠቡ። ልብሳቸው ያለቀና የተቀዳደደ ስለነበር፡ አዲስ ልብስ ቀርቦላቸው ለበሱ። በሰንሰለት ሳይታሰሩ በምቹ ከፍል ውስጥ ቢጠበቁም እንኳ፣ ራስ ጉግሣ እንዳያመልጧቸው ከልጅ ደስታ ዳምጠው ጋር ሲወያዩ እየሰሙ ስለ ሕይወታቸው ይሰጉ ነበር። ከአዲስ አበባ በተላለፈው ትእዛዝ ግንቦት 4 ቀን በምሥጢር ወደ አምባላጌ ተወሰዱና አምባላጌ ሆነው ተከታዩን የመንግሥት ትእዛዝ ይጠባበቁ ጀመር። የልጅ ኢያሱ መያዝ ግን ለማዕከላዊ መንግሥት ታላቅ ዕፎይታና የምሥራች ሆነለት።” (አቶ ጐበዜ ገጽ 121-122)

ራስ ጉግሣ አቤቶ ኢያሱን ለተፈሪ መኰንን በግንቦት 13 ደሴ ላይ ካስረከቧቻው በኋላ ተማራኪው ወደ ሸዋ ፍቼ አውራጃ በግዞት እንዲቀመጡ ተደረገ። ተማራኪው ልጅ ኢያሱ ግን በ1924 ከፍቼ አምልጠው ጐጃም ገቡ፣ እንዴት እንዳመለጡም ለራስ ኃይሉ ተክለኃይማኖት ደብዳቤ ጽፈው ስለነበር እነ ራስ ተፈሪም ነገሩን ስለደረሱበት ወድያውኑ ራስ ኃይሉ በቍጥጥር ስር እደንዲውሉና ወደ ወለጋ እንዲጋዙ ሲያደርጉ ልጅ ኢያሱንም በደጃዝማች አበራ ካሣ (የኤርትራ እንደራሴ ለነበሩት የራስ አስራተ ካሣ ወንድም) ተፈልገው እንዲያዙ ጥብቅ ትእዛዝ አስተላለፉ። ልጅ ኢያሱ ግን በደጃዝማች አበራ ሳይሆን የራስ ኃይሉ ዘመድ በሆኑት ፊተውራሪ ገሠሠ በለው የተባሉትን ነው የተያዙት። ፊተውራሪ ገሠሠ ልጅ ኢያሱን

ጐጃም ውስጥ ከያዝዋቸው በኋላ ለራስ ደስታ ዳምጠው አስረከቧቸውና አቤቶ በባቡር ወደ ድሬ ዳዋ ከዛም ወደ ግራዋ/ጋረሙለታ ተወሰዱ።

ልጅ ኢያሱ ጋረሙለታ ውስጥ ለዓራት ዓመታት በእስር በቆዩበት ግዜ ከዘበኞቹ ሌላ በጥብቅ ሁኔታቸውን እንዲከታተሉ ትእዛዝ የተሰጣቸው ብላቴን ጌታ ሎረንሶ ታእዛዝና አባ ሓና ጅማ ናቸው። በ1928 ግን ጣልያን ኢትዮጵያን ስለወረረች ጣልያኖችም ልጅ ኢያሱን ከእስር ለማወጣት እቅድ አላቸው የሚል ወሬ ስለተነዛ ተፈሪ መኰንን (አሁን ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ንጉሠ ነገሥት) ጉዳዩ በጣም አሳስቧቸው ስለነበር ልጅ እያሱን ወደ ሌለ የግዞት ቦታ ለመውሰድ እቅድ ነበራቸው የሚል እምነት አለኝ። ነገር ግን በዝያን ግዜ በሓረር አከባቢ ልጅ ኢያሱ እስር ቤት ወስጥ ተገደሉ ገዳዮቻቸውም ሎሬንሶ ታእዛዝና አባ ሃና ናቸው የሚል ወሬ ተነዛ። ሎረንሶ ታእዛዝ ወሬውን በግዜው ስያስተባብሉ እስር ቤት እያሉ እንዳዩዋቸውና እንዳዘኑላቸው ገልጸዋል። በሌላ በኩል ደግሞ ልጅ ኢያሱ በልዩ ባቡር ወደ አዲሰ አባባ መወሰዳቸውን ነበር የተወራው፣ ይህ ወሬ ቀጥለን ከምናየው የዓይን ምስክርነት ጋር ስናገናዝበው እውነትን ያዘለ ይመስላል። ልጅ ኢያሱ በበኩላቸው ኢጣልያ ኢትዮጵያን መውረርዋን ከሰሙ በኋላ እንዲህ ብለው ተናገሩ ይባላል፦ "...ታማኝ ብሆን ኖሮ እንደማንኛውም ተራ ወታደር ጠመንጃ አንግቤ በጦሩ ግምባር ለመሰለፍ በወደድሁ ነበር። የሆኖ ሆኖ ጉዳዩ አስጊ ነውን? ዳዊቴን ስደግምና ጸሎቴንም በማቀርብበት ግዜ ሁሉ ስለ ኢትዮጵያ ነጻነት ጉዳይ ሳልማፀን ቀርቼ አላውቅም።"

አጼ ኃይለሥላሴ ወደ ማይጨው ጦር ግምባር ዝግጅት በሚያደርጉበት ግዜ ልጅ ኢያሱ ገነተ ልዑል ቤተ መንግሥት ውስጥ በእስርነት እንደቆዩና እዛው እንደተገደሉ የጠረጠሩና የመሰከሩ ሰዎች አሉ። ከነሱም አንዱ በማርቆስ ቤተ ክርስትያን አገልጋይ የነበሩ ቄስ ገብረመድኅን የሚባሉ ናቸው። አቶ ጐበዜ በመጽሓፋቸው እንደጠቀሱት እኚህ ቄስ ለአቶ ሎረንሶ ታእዛዝ ያጫወቷቸውን ብላቴን ጌታም በበኩላቸው እንደመዘገቡት በዚህ መልክ ቀርቧል፦

"በቅዱስ ማርቆስ ቤተ ክርስትያን ትይዩ የዱክ ቤት ይባል በነበረውና አሁን /የሕግ ከፍል ትምህርት ቤት/ በሆነው ሕንጻ ሰገነት ላይ አንድ እጆቹ በሰንሰለት የታበተ ሰው ከቀትር በኋላ ዘወትር ሲመላለስ እናየው ነበር። እንዲሁም ለጥቂት ወራት ወደዚሁ ቤት ሲገባ እናይ ነበር። ነገር ግን ጃንሆይ (ንጉሡ) ወደ ጦርነቱ ከመዝመታቸው በፊት ሌሊቱን ጸሎተ ፍትሐት እንድናደርግ ታዘዝን። ሆኖም የሟቹ ስመ ክርስትና የሚነግረን ሰው አልነበረም። ከዚህ በኋላም ያ ሰውዬ ይመላለስበት የነበረው ሰገነት ላይ ማንም አልታየም። እኛም የሞቱት ልጅ ኢያሱ እንደሆኑ ገመትን።" (አቶ ጐበዜ ገጽ 151)

በዚሁ በተባለው ጸሎተ ፍትሓት ስነሥርዓት እተጌ መነን እንደ ሓዘንተኛ ተቀምጠው ነበር፣ ጃንሆይ ደግሞ ከት ብለው አለቀሱ ይባላል። እንደሚታወቀው ሁሉ ልጅ እያሱ የእተጌ መነን አጎት የወይዘሮ ስሂን ሚካኤል ወንድም ናቸው፣ መነንን ለጃንሆይ የዳሩላቸው ደግሞ እሳቸው ናቸው። በጣም የሚገርም ነው! የሚስቴ አጎት ነው በድህና ግዜም እንደ ወንድማማች አብረን አድገናል በሚል የክርስትያን መንፈስ እንኳ ምሕረት አይደረግም እንዴ? አልተደረገም! ሌላ በጣም የሚገርመው ግን ቄስ ገብረመድኅን እንደመሰከሩት 'የክርስትና ስም' ብቻ አይደለም የጠፋው፣

ሬሳውም በፍትሐቱ ግዜ አልነበረም፣ የት እንደተቀበረም የሚታወቅ ነገር የለም። እስካሁን ድረስ ባልተረጋገጠ ወሬ ስለ ልጅ ኢያሱ ሬሳ የሚያውቁ ባላምበራስ (በኋላ ራስ) አበበ አረጋይ ብቻ ናቸው የሚል ነው። ብያንስ ብያንስ ዶማ ተሸካሚውና ጉድጓድ ቆፋሪው፣ እንዲሁም የቀብሩን ንድፍ ያወጡት ወንጀለኞች ያውቃሉ። ማን ያርዳ የቀበረ፣ ማን ያውራ የነበረ እንዳይባል ደግሞ ሁሉ ነገር በከፍተኛ ሚስጢር ነው የተካሄደው። ነገር ግን ልጅ ኢያሱ ከሞቱ 72 ዓመት ብቻ ስለሆነ በዛን ግዜ የነበሩ አሁን በሕይወት ያሉና የምያውቁ ቢናገሩ ላለውና ለመጪው ትውልድ ቅርስ እንደመተው ነው የሚቆጠረው።

ትንሽ አስቸጋሪ ሊሆን የሚችለው በዛን ግዜ ያውቃሉ ተብለው የሚጠረጠሩ ግለሰቦች እንደ ራስ ኣበበ አረጋይ፡ እንደ አባ ሓና ጅማ የመሳሰሉት በ1953 ዓ.ም. በመንግስቱ ንዋይ መፈንቅለ-መንግሥት እዛው ልጅ ኢያሱ በሞቱበት (በተገደሉበት) ማለትም ገነተ ልዑል ቤተ መንግሥት ውስጥ ተገድለዋል። ከሁሉም በላይ ውስጠ-ሚስጢሩን ያውቃሉ የተባሉትን አጼ ኃይለሥላሴም ዕጣው ደርሰዋቸው ከየካቲት 1966 የኢትዮጵያ አብዮት ፍንዳታ በኋላ በወታዶሮቹ እጅ ላይ ወድቀው ተዋርደውና ተንገላተው ሞቱ። ስለዚህ ምናልባት ለወደፊት በጥናትና ምርምር ስለ ልጅ ኢያሱ አሟሟች ካልታወቀ በስተቀረ ያውቃሉ የተባሉትን ሰዎች አልፈዋል።

ታሪክ ግን ለዘልአለም ይኖራል! እንድያውም አንዳንድ ግዜ ‘ታሪክ ራሷን ትደግማለች’ የሚለውን አነጋገር በመጠኑም ቢሆን እውነትነትን ያዘለ ነው። በመጽሓፌ ውስጥ እንደጠቀስኩት ስድስት ኪሎ ደም የጠማው ጋኔን የሰፈረበት አከባቢ ነው ማለት ይቻላል። ከፍ ብለን እንዳየነው ልጅ ኢያሱ እዛው ነው የተገደሉት፣ በመንግሥቱ ንዋይ ግዜም የብዙ ኢትዮጵያውያን መኳንንት ደም በዚሁ ቦታ ፈሰሰ፣ የፋሺስት ጣልያን የነግራዝያኒ ወታደሮች ደግሞ በብዙ ሺ የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን በግፍ የጨፈጨፉት በዚሁ በስድስት ኪሎና ዙርያውን ነው፣ በ1962 በኢትዮጵያ አቆጣጠር ወይም በ1969 መጨረሻ በአውሮጳ አቆጣጠር ጀግናው ጥላሁን ግዛው በመንግሥት ትእዛዝ ከተገደለ በኋላ ተማሪዎች የልቅሶና የቀብር ሥነስርዓት እንዲደረግለት ከወሰኑ በኋላ ሬሳው መጀምርያ ወደ ማርቆስ ቤተክርትያን (የልጅ ኢያሱ ፍትሐት የተደረገበት) ነበር የተወሰደው፣ ቀጥሎ ለቀብሩ ዝግጅት ወደ አዲሱ የአርት ህንጻ ፊት ለፊት ባለው ሜዳ ውስጥ እንዲያርፍ ተደረገ፣ ቀጥሎ የክብር ዘበኛ ጥይቶች መዝነብ ጀመሩ፣ ተማሪዎቹም በሚበታተኑበት ግዜ ብዙ ቆሰሉ፡ የሞቱም ነበሩ፣ ከመዓቱ የተሰወሩና ጥይት ሳይመታቸው ያመለጡም ነበሩ፣ ከነዚሁ አንዱ እኔ ነበርኩኝ። በቅርቡም ቢሆን የለመደው ጋኔን በስድስት ኪሎ አከባቢ ደም ሳይጠጣ አልቀረም።

ኢጋጣሚ አብዮቱ እንደፈነዳ፡ ሰለማዊ ሰልፎች ሲካሄዱና ወታዶሮቹ በጂፕ መኪኖቻቸው ወድያና ወዲህ ሲሯሯጡ እኔ ከሽሮ ሜዳ ተነስቶ ወደ ቄራ የሚሄደውን 16 ቊጥር አንበሳ አወቶቡስ ይዤ በምኀዝበት ግዜ ልክ አራት ኪሎ ታላቁ ቤተ መንግሥት አከባቢ እንደደረስን ብዙ ሰዎች ተሰብስበው ‘ሌባ ሌባ’ ሲሉ ሰማሁኝ፣ ከነዚህ ጨፋሪዎች ባሻገር በዓይኔ ስቃኝ ደግሞ ጃንሆይ በወታደሮች ተይዘው ወደ ቮልክስዋገን ሲገቡ አየሁኝ፣ በጣም በመገረምም ‘እንደ ቀን ጣይ የለም’ በማለት አሰላሰልኩኝ። ለነገሩ፡ የጃንሆይን ሥርዓት ለማውደቅ ከታገሉት ተማሪዎች አንዱ ነበርኩኝ፣ የየካቲት አብዮትም አመጣጥ ደግፍያለሁ። ነገር ግን

ንጉሡ ነገሥቱ ተዋርደው ቮልክስዋገን ውስጥ ሲገቡ ባየሁ ግዜ ኣዘንኩላቸው! በደርግ እጅ ወድቀው መሞታቸውን (መገደላቸውን) ከሰማሁኝ በኃላ ደግሞ የበለጠ አዘንኩላቸው። አሁን ይኸንን ጸሑፍ በማዘጋጅበት ግዜ ደግሞ ምናልባት የኢያሱ ደም ይሆን በእንዲህ ዓይነት ክፉ አወዳደቅ የጣላቸው የሚል ሓሳብ ከፊቴ ተደቀነ! ይኸንን የመሰለ አመለካከትና ትርጓሜ ከብዙ ሰዎች ዘንድ ሊፈልቅ ይችላል፣ ወይም በአንጻሩ ፍጹም የተለየ ሓሳብ ያላቸው አንባብያን ሊኖሩ ይችላሉ፣ ስለሆነም መድረኩ ክፍት ነውና ሓሳቦቹ ቢቀርቡ ደስታውን አልችለውም።

አኔ በበኩሌ የማቀርበው ሐሳብ ቢኖር ግን አጼ ኃይለሥላሴ በበጎ አድራጎታቸው ተመስግነው፡በጥፋታቸው ተወቅሰው በታሪክ ማስታወሻዎች ስማቸው መቀመጥ ይኖርበታል የሚል ነው። ቀደም ብየ እንደጠቀስኩት በ1995 ዓ.ም. በጻፍኩት መጽሓፍ ውስጥ የጃንሆይ ጥንካሬና ድክመት ሚዛናዊ በሆነ መንገድ አስቀምጬዋለሁ። ልጅ ኢያሱም ልዩ መታሰብያ ተደርጎላቸው በኢትዮጵያ የታሪክ ሰነድ ውስጥ መስፈር አለባቸው። ምንም እንኳ በሥልጣን የቆዩበት ግዜ በጣም አጭር ቢሆንም ኢትዮጵያን ለማሰልጠን የነበራቸው ራእይና ፍላጎት እንዲሁም ከፍተኛ ያገር ተቆርቋሪነታቸው ጠንካራ ጎናቸውን ስለምያንጸባርቁ ብያንስ ብያንስ ያሁኑ ትውልድ ልያስታውሳቸውና ሓወልት ሊሰራላቸው ይገባል።

ምስጋና፡ ለአቶ ጕበዜ ጣፈጠ የ <u>አባ ጤና ኢያሱ</u> ደራሲ፣ ለአቶ ዘውዴ ረታ የ <u>ተፈሪ መኰንን፡ ረዥሙ የሥልጣን ጉዞ</u> ደራሲ፣ እንዲሁም ለአቶ ኪዳኔ አለማየሁ የአቶ ጕበዜ መጽሓፍ ለላኩልኝ እጅግ የላቀ ምስጋናየን አቀርብላቸዋለሁ።

All Rights Reserved © copyright IDEA, Inc. 2007 Dr. Ghelawdewos Araia can be contacted for constructive and educational feedback at dr.garaia@africanidea.org